# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ነገረ ማርያም

ነገረ ማርያም ማለት ስለ ድንግል ማርያም የሚናገር በድንግል ማርያም ላይ የተመሠረተ ትምህርት የድንግል ማርያም ነገር ማለት ሲሆን የቃሉ ትርጉም፣ ስለ ድንግል ማርያም ልደት፣ ልሕቀት እመአምላክ ወላዲተ አምላክነት፣ ጸጋ፣ ክብር፣ ሰላምታ የሚናገረው የቤተክርስቲያናችን መጽሐፍም ነገረ ማርያም ይባላል።

ይህንን አነስተኛ ጽሑፍም ነገረ ማርያም ያልኩት ስለድንግል ማርያም ልደት፣ ልሕቀት፣ ቅድስና፣ ክብር ወዘተ የተቻለኝን ያህል ለመጻፍ ነው።

1. ልደተ ማርያም፡- እመቤታችን ድንግል ማርያም እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ከሐናና ከኢያቄም በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በስዕለት ወደ እግዚአብሔር ሲማጸኑ ከቆዩ በኋላ በብሥራተ ገብርኤል በፈቃደ እግዚአብሔር ነሐሴ 7 ቀን ተጸንሣ ግንቦት 1 ቀን ተወለደች፤ በተጸነሰችበት ጊዜ ተአምራት እንደተደረገ በነገረ ማርያም ተጽፏል። ሐናና ኢያቄምን በተደረገው ተአምራት ምክንያት አይሁድ ቀንተው ስላሳደዷቸው እመቤታችን በሊባኖስ ተራራ ተወልዳለች አባቷ ሰሎሞን "ሙሽራዬ ሆይ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነይ፣ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነይ" (መኃ 4፥8) ብሎ የተናገረው ተፈጽሟል (ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ነገረ ማርያም፣ ትርጓሜ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ወንጌል ይመልከቱ)።

2. ልሕቀት (እድገቷ)፡- ስለእመቤታችን አስተዳደግ በምሳሌና በትንቢት ካልሆነ በቀር በታሪክ መልክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ



የተጻፈ ምንም ነገር የለም። ስለእድገቷም፣ ስለቤተሰቦቿም፣ የተጻፈ ነገር የለም። የእነማን ልጅ ናት? የት ተወለደች? መቼ ተወለደች? የት አደገች? ወዘተ ለሚባሉት ጥያቄዎች ምንም መልስ አይሰጥም ነገረ ማርያም ወደሚባለው መጽሐፍ ትረካ ስንሄድ ግን የታሪክ መጽሐፍ እንደመሆኑ አብራርቶ ጽፏል፤ በነገረ ማርያም እንደተጻፈው ሁሉ ድንግል ማርያም በተወለደች በ3 ዓመቷ ወላጆቿ በተሳሉት መሠረት ለቤተ እግዚአብሔር ስለሰጧት ለ12 ዓመታት በቤተ እግዚአብሔር ኑራለች ይህንንም በሚመለከት ቅዱስ ሕርያቆስ በቅዳሴው "ኦ ድንግል አኮ በተላህዮ ዘልሕቂ ከመ አዋልደ ዕብራውያን እለ ያገዝፋ ክሳዶን አላ በቅድስና ወበንጽሕ ውስተ ቤተመቅደስ ነበርኪ" ማለት "ድንግል ሆይ ክሳደ ልቡናቸውን እንደአደነደኑ የዕብራውያን ቆነጃጅት በቀልድ በጨዋታ ያደግሽ አይደለሽም በቅድስናና በንጽሕና በቤተመቅደስ ውስጥ ተቀመጥሽ እንጂ" ብሏል "ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምዒ ዕዝነኪ ርስዒ ሕዝበኪ ወቤተ አቡኪ እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ እስመ ውእቱ እግዚእኪ" ማለት "ልጄ ሆይ ስሚ እዪ ጆሮሽንም አዘንብዪ ወገንሽንም የአባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወዷልና እርሱ ጌታሽ ነውና" (መዝ 44፥10) ያለው ቃል ለዚሁ ለእድገቷ ተሰጥቶ ይተረጐማል ምሥጢሩ ግን ብዙ ስለሆነ ትርጓሜ ዳዊት መመልከት ይጠቅማል እንግዲህ በአጭሩ የእመቤታችን ዕድገት ቤተ እግዚአብሔር ውስጥ ነው።

ሰላምታ (የገብርኤል ሰላምታ)፡- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ያቀረበላትን ሰላምታ መሠረት በማድረግ እናት ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ዘወትር ድንግልን ሠላም ትላታለች ይህ የመልአኩ ገብርኤል ሰላምታ ሞት ለተፈረደበት ለሰው ልጅ ባሕርይ ግሩም ወንጌል (የምሥራች) ነው።

ከዚህ የተነሣ መልአኩን ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ተዋሕዶን የሚሰብኩ ቅዱሳን "መጋቤ ሐዲስ" የመጀመሪያው ወንጌል ሰባኪ (መምህር) ይሉታል።

ድንግል ማርያምንም በመልአኩ ሰላምታ ዘወትር ሰላም እንድንላት ሥርዓት ሠርተው አልፈዋል ከዚህ በማስከተል ሠላምታዎቹን በዝርዝር እንጽፋለን።

4. ደስ ይበልሽ፡- (ሉቃ 1፥28) መልአኩ ወደ ድንግል ቀርቦ መጀመሪያ የተናገረው "ደስ ይበልሽ" በማለት ነበር ወንጌል ማለት የምሥራች ማለት ነው። የምሥራች ማለት የደስ ደስ ማለት ነው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ በመምጣት ድንግልን ደስ ይበልሽ አላት ይህ ለድንግል ማርያም ግሩም ጸጋ ነው። ምክንያቱም የአዳም ተስፋ በእርሷ በኩል እንዲፈጸም እግዚአብሔር ወስኗልና። ሞት የተፈረደበት ለዘመናት እንዲያለቅስ፣ እንዲፈርስ፣ እንዲበሰብስ አእምሮውን ንባቡን አጥቶ፣ በሰው ትከሻ ተጓጉዞ ወደ መቃብር እንዲጣል የተፈረደበት የሰው ልጅ ባህርይ በድንግል ማርያም በኩል ደስ ይበልህ ተባለ፣ ስለዚህ የሰው ዘር በሙሉ የድንግል ደስታ ደስታው ስለሆነ "ምልዐተ ጸጋ ደስ ይበልሽ" እያለ ይዘምርላታል፣ ድንግል የደስታ መፍሰሻ እንድትሆን በአልቃሻው ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ወስኗልና በመሆኑም ድንግል ማርያምን ደስ ይበልሽ እያለች ቤተክርስቲያን የምታመሰግንባቸውን ቃላት እንመልከት ቅዱስ ኤፍሬም የመልአኩን ሰላምታ መሠረት በማድረግ "ተፈስሒ ኦ ቤተልሔም ሐገሮሙ ለነቢያት - የነቢያት ሐገራቸው ቤተልሔም ደስ ይበልሽ" (የሰኞ ውዳሴ ማርያም) "ተፈሥሒ ኦ ወላዲተ እግዚእ ሐሤቶሙ ለመላእክት - የመላእክት ተድላ ደስታ ጌታን የወለድሽ ደስ ይበልሽ" ወዘተ እያለ እመቤታችንን ሰላም ብሏታል እኛም በውዳሴው ደስ ይበልሽ በማለት ሰላምታ እናቀርባለን።



ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለድንግል ያለውን ክብር ሲገልጽ "እግዚአብሔር ቃል ነፍስን ሥጋን ከአንቺ ነሥቶ ሰው የሆነ ሙሽራ ከጫጉላው እንዲወጣ ከአንቺ የተገኘ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ . . . የጠፋ በግ አዳምን የፈለገው ቸር ጠባቂ ከአንቺ የተገኘ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ፣ ከአንቺ ያደረ ምድር ቅድስት ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ፣ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ እግዚአብሔርን የወለድሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ፣ አማኑኤልን የወለድሽ ማርያም ሆይ ደስ የበልሽ ወዘተ" በማለት ያመሰግናት እንደነበር ተጽፏል። ሃይማኖተ አበው ዮሐንስ አፈወርቅ ገጽ253 ክፍል 26 ቁ.35-39 ይመልከቱ። ቤተክርስቲያንም "ሙሐዘ ፍስሐ-የደስታ መፍሰሻ" በማለት ታመሰግናታለች፣ ቅድስት ድንግል ማርያም በመልአኩ ብሥራት በግብረ መንፈስ ቅዱስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድን ከጸነሰች በኋላ "ተአብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ወትትሐሠይ መንፈስየ በአምላኪየ ወመድኃኒየ-ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች" በማለት ደስታዋን ገልጻለች። ለድንግል ማርያም የሆነው ደስታ ሁሉ የሰው ልጆች ደስታ ነው በድንግል ማርያም በኩል ደስታ ለሰው ሁሉ ስለደረሰ ድንግል ማርያም የደስታ መፍሰሻ ናት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ደስታ እንዴት ወደ ፍጥረት ሁሉ እንደደረሰ ሲገልጽ ጌታ ሲወለድ በጨለማ ለነበሩ እረኞች "ለሕዝብ ሁሉ ታላቅ ደስታ የሚሆን የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" አሏቸው ቅዱሳን መላእክት ይለናል ሐዋርያው። ቅዱስ ጳውሎስም የድንግልን ልብ በደስታ በሐሴት የሞላው ክርስቶስ የእኛም ተድላ ደስታ መሆኑን ሲጠቁም "ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ" (ፊልጵ4፥4) በማለት ጽፎልናል ተፈሥሒ ተፈሥሒ እያለ ያመሰገናት ቅ/ኤፍሬም የድንግል ማርያም ደስታ የሰው ሁሉ መሆኑን ሲጽፍ "ተፈሣሕ ወተሐሠይ ኦ ዘመደ እጓለ እመሕያው እስመ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም ወመጠወ ወልዶ ዋሕደ ከመ ይኅየው ኲሉ ዘየአምን ቦቱ እስከ ለዓለም - በእርሱ የሚያምን ሁሉ እስከ ዘለዓለም

ይድን ዘንድ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለሙን እግዚአብሔር ወዶታልና የሰው ልጅ ሁሉ ደስ ይበልህ" አለ እንዲሁም "ትትፌሣሀ ወትትሐሠይ ኩሉ ነፍሳተ ሰብእ የሰው ልጅ ሰውነት ሁሉ ፈጽሞ ደስ ይላታል" አለ እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው ድንግልን ደስ ይበልሽ የማይል በአዳም የተነጠቀው ተድላ ነፍስ በክርስቶስ ያልተመለሰለት ብቻ መሆን አለበት ድንግልን ደስ ይበልሽ ባልን ቁጥር እኛም የተድላ የደስታዋ ተካፋይ መሆናችንን ተገንዝበን በገብርኤል ሰላምታ ደስ ይበልሽ እንበላት።

5. <u>ሰላምታ "ጸጋን የተሞላሽ ሆይ"፡-</u> መልአኩ ጸጋ እግዚአብሔር ላንቺ ምሉዕ ሆኗልና ደስ ይበልሽ በማለት አከበራት ፍጥረት ሁሉ እንደሚያውቀው የሰው ልጅ ከጸጋ እግዚአብሔር ተለይቶ ሐፍረቱን የሚሸፍንበት አጥቶ ይንገላታ እንደነበር ግልጽ ነው። የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ሕይወቱን አጥቷል እግዚአብሔርን አጥቷል። ኤደን ገነትን አጥቷል ፍጹም ከጸጋ እግዚአብሔር ተራቁቷል፤ አሁን ግን በቅዱስ ገብርኤል በኩል የምንሰማው ከሰው ልጆች መካከል አንዷ ለሆነች ለሰው ልጆች የባሕርይ መመኪያ ለድንግል ማርያም "ጸጋን የተመላሽ" በማለት ሲያበሥራት ስንሰማ ያስደስታል ይህ ጸጋ በድንግል ማርያም ሳይወሰን ለፍጥረት ሁሉ ይደርሳልና።

ድንግል ማርያም ምልዕተ ጸጋ ናት ጸጋውም ለፍጥረት ሁሉ ከተሰጠው ጸጋ ይበልጣል ከነቢያት ጸጋ የድንግል ጸጋ ይበልጣል እነርሱ ስለ እግዚአብሔር ሰው መሆን ተናገሩ እርሷ ግን በጥበበ - እግዚአብሔር እርሱን ወለደችው ከሐዋርያትም የድንግል ጸጋ ይበልጣል እነርሱ ከእርሷ የተወለደውን ኢየሱስን ለፍጥረት ሰበኩ እርሷ ግን ወልዳ አሳደገችው፤ ከቤተክርስቲያን ጸጋ የድንግል ጸጋ ይበልጣል ለቤተክርስቲያን ልሳን፣ ትንቢት፣ ስብከት . . . ተሰጥቷል ድንግል ባለቤቱን ጸንሳ ወለደችው፣ በእርሷ በኩል የመጣው የእግዚአብሔር ጸጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሁሉ



ተሰጠ ኢሳይያስ "ሕጻን ተወልደ ለነ ወልድ ተውህበ ለነ" አለ ማለትም "ሕጻን ተወለደልን ወንድ ልጅ ተሰጠን" (ኢሳ 9፥6) ኢየሱስ ክርስቶስን የሰው ዘር የተቀበለበት እጁ ድንግል ናት የሰው ልጅ ባህርይም በድንግል ተጀምሮ በእርሷ ጸጋ የተሰጠው በመሆኑም የፍጥረት ሁሉ የባህርይ መመኪያ እመ አምላክ ሆነች።

6. <u>ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፡-</u> (ሉቃ 1፥28) ሦስተኛው የሰላምታ ቃል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው የሚል ነው። ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በረድኤት እንጂ በኩነት ከሰው ጋር ያልነበረ አምላክ በአዳምና በሔዋን በደል ከሰው የተለየ አምላክ ከአንቺ ጋር ነው የሚለው ሰላምታ መንፈስን የሚፈውስ ነው። አካል ዘእም አካል ባሕርይ ዘእም ባሕርይ ከአብ የተወለደ ወልድ ከድንግል ነፍስን ሥጋን መንፈስን ነሥቶ ስለተወለደ እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ከድንግል ጋር ነበር። ከድንግል ጋር እንደሆነ የተነገረው የሰላምታ ቃል ለእኛም ጭምር ስለሆነ የመልአኩን ሰላምታ "እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ" እያልን ለድንግል ስናሰማ እኛም ደስ ይለናል (ኢሳ 7፥14) ከድንግሊቱ የሚወለደው አማኑኤል ይባላል በተባለው መሠረት ሲወለድ አማኑኤል ተባለ። አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው። ከድንግል ጋር የሆነ ጌታ ከእኛም ጋር ነውና ደስ ሊለን አግባብ ነው። በስሙ ስንሰበሰብ (ማቴ 18፥20)፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእኛ ጋር ነውና (ማቴ 28፥28-29) ይህም ብሥራት ለድንግል መነገሩ የድንግል ባህርይ ባህርያችን ነውና የእኛም ብሥራታችን ነው። ይህንንም ቅዱስ ኤፍሬም "ዓቢይ ውእቱ ክብር ዘተውህበ ለከ ኦ ገብርኤል መልአክ ዜናዊ ፍሡሐ ገጽ ሰበከ ለነ ልደተ እግዚእ ዘመጽአ ኀቤነ" ማለትም "ወደእኛ የመጣ የጌታን ልደት የሰበክልን ፍሡሐ ገጽ መልአክ ገብርኤል ሆይ ላንተ የተሰጠህ ክብር ታላቅ ነው" ማለት ነው። ኤፍሬም "ሰበከ ለነ" ማለቱ ልደቱ፣

ብሥራቱ የሰው ልጅን ሁሉ እንድሚመለከት ለመግለጽ ነው። ከድንግል የተወለደው ልዑል አምላክ ከእኛ ጋር ነውና ደስ ይበለን እኛም ድንግልን "እግዚአብሔር ምስሌኪ" እያልን ሰላም እንበላት። በሌላም ገጽ ቅ.ኤፍሬም የመልአኩ ቃል (ብሥራት) ለሕዝብ ሁሉ መሆኑን ሲገልጥ "ተፈስሒ እስመ ተወከፍኪ ቃሎ ለመልአክ ፍስሐ ኩሉ ዓለም - የዓለሙን ሁሉ ተድላ ደስታ የመልአኩን ቃል ስለአመንሽ ደስ ይበልሽ" አለ።

አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፡- (ሉቃ1፥28) መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ደስ ይበልሽ ካለ በኋላ የተናገረው ሰላምታ "የተባረክሽ ነሽ" የሚል ነበር የሰው ዘር በመጀመሪያዎቹ ሰዎች በደል ምክንያት "በጽነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ በጭንቅ ትወልጃለሽ... ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን በሕይወት ዘመንህ በድካም ከእርሷ ትበላለህ እሾህና አሜከላን ታበቅልብሃለች የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ ወደመጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ" ተብሎ ተረግሞ ነበር (ዘፍ3፥16-21) ይህ ከባድ መርገም በሰው ሕይወት እንዲበዛና እንዲከሰት ምክንያት የሆነውን አውሬ እራስ የሚቀጠቅጥ ልጅ እንደሚወለድ ለአዳም እግዚአብሔር ቃል ገባለት (ዘፍ3፥15-16) ለአብርሃም ደግሞ በዘሩ የምድር አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ ተስፋ ሰጠው (ዘፍ12፥4)፤ ለይስሐቅም ለያዕቆብም ለአበው ሁሉ ይህ ቃል ኪዳን ተሰጣቸው በመጨረሻ ላይ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያስወግድ የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጥ ቡሩክ የማሕጸኗ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወለድባት ቅድስት ማርያም ቡርክት ነሽ ተባለች። ቡርክት ማለትም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት የበረከት እናት ማለት ነው። የማሕጸንዋ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስም ቡሩክ ነው። ቡሩክ ይባላል (ሉቃ1፥42) እርሱ ቡሩክ ሳለ ማለትም



መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የሚያድል ሆኖ ሳለ "በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማንዋጀን" (ገላ3፥13) ተብሎ እንደተጻፈ ስለእኛ ተሰቅሎ ከእርግማን አዳነን እግዚአብሔርም በልጁ በክርቶስ ኢየሱስ በምድራውያንና በሰማያውያን በረከት ባረከን (ኤፌ 1፥2,4) ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለተኛ ሲመጣ ከተባረከችው ድንግል የተወለደውን ቡሩኩን የማሕፀኗን ፍሬ አምኖ በመስቀሉ እርግማኑ የተወገደለት መሆኑን በእርግጠኛነት የተቀበለ "እናንተ የአባቴ ብሩካን ወደ እኔ ኑ" (ማቴ25፥34) ብሎ ከሚጠራቸው ጋር ይቆጠራል "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ" (ኤፌ 1፥3)።

8. ብሥራተ መልአክ፡- ማለት መልአኩ ከሰላምታው በማከታተል አካላዊ ቃልን እንደምትወልድ "እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱም ታላቅ ነው ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል በያዕቆብ ቤትም ለዘለዓለም ይነግሣል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም" (ሉቃ1፥30-34) በማለት አበሠራት ድንግልም ይህ እንዴት ይሆናል? ወንድ ስለማላውቅ አለችው።

9. ጽንሰተ ቃለ አብ፡- ጽንሰተ ቃለ አብ (አካላዊ ቃልን መጽነስ) እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አካላዊ ቃልን የጸነሰችው የ15 ዓመት ልጅ በሆነችበት ወቅት እንደነበር ነገረ ማርያም የሚባለው መጽሐፍ ይተርካል። ወንጌላዊ ሉቃስም ብብሥራተ መልአክ በፈቃደ አምላክ በግብረ መንፈስ ቅዱስ መጽነሷን ይናገራል (ሉቃ 1፥26-38)።

10. ግብረ መንፈስ ቅዱስ፡- ከላይ ለተጠየቀው መልሱ ግብረ መንፈስ ቅዱስ (የመንፈስ ቅዱስ አሠራር) የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ነገራት በተጨማሪም የዘመዷን የኤልሳቤጥን ከእርጅና በኋላ መጽነስ ነገራት በተጨማሪም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ብሎ መለሰላት ድንግልም ለዚህ ቃል ተሸነፈች እንደ ሰው ምድራዊ ሐሣብ እንደተፈጥሮ ሥርዓት ሳይሆን እንደቃልህ ይሁንልኝ ብላ በማመኗ አካላዊ ቃል በማዕምንት ድንግል ማኅፀን አደረ። ዛሬም እኛ እንደ ድንግል ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ አምነን ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ የሚነገሩትን ነገሮች አሜን ብለን ብንቀበል ለእግዚአብሔር ቃል ብንታዘዝ ታላቅ ነገር ይደረግልናል።

ድንግል እንደቃልህ ይሁንልኝ (ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ) በማለቷ የማይቻለውን ቻለች፣ የማይወሰነውን ወሰነች "ጾርኪ ዘኢይጸወር አግመርኪ ዘኢይትገመር ወአልቦ ዘያገምሮ ምንትኒ" ብሎ ቅዱስ ኤፍሬም እንደተናገረ አምላክም ሞት የተፈረደበትን ባህርየ ሰብእ በመንሣቱ ሰው ከበረ ካሳም በማኅጸን ተጀመረ በኀቱም ድንግልና እንበለ ሩካቤ (ያለግንኙነት) ተጸንሷልና መለኮታዊነቱን ገለጸ "ወዘእንበለ ይትቃረቡ ተረክበት ጽንስተ እንዘ ውስተ ማኅፀና - ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች" ተብሎ እንደተጻፈ (ማቴ 1፥18-19)።

11. ልደተ ቃለ አብ፡- በብሥራተ መልአክ የተጸነሰው ቃለ እግዚአብሔር ወልድ እንበለ ተፈትሆ ማኅፀን በሕቱም ድንግልና እንደተጸነሰ በሕቱም ድንግልና ተወለደ፣ የተወለደውም በኢየሩሳሌም ቤተልሔም በሚባለው ቦታ በከብቶች በረት ተወለደ በመወለዱም የሰላም መዝሙር በመላእክትና በሰዎች ኅብረት ተዘመረ እርሷም እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ፣ እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ተባለች (ሉቃ 2፥1-13)



12. ዘለዓለማዊ ድንግልና፡- "በሀሣብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ" ይህ ድምፅ እናት ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን በገብርኤል ሰላምታ ድንግል ማርያምን ሰላም ስትል የምታስደምጠው የምስጋና (የሰላምታ) ድምፅ ነው። በዚህ ላይ ስለድንግልናዋ በደንብ እንከታተል የእመቤታችን ድንግልና ልዩ ድንግልና ነው። ልዩም የሚያደርገው የሥጋም የኅሊናም ስለሆነ ነው። የሰው ልጆች ሁሉ በሥጋ ድንግል ቢሆኑም በኅሊና ድንግል አይሆኑም ማንኛውም ሰው ከጋብቻ በፊት ድንግል ቢሆን ከዚያ በኋላ ድንግል አይሆንም። ድንግል ቅድመ ጸኒስ (ከመጽነስ በፊት)፣ ጊዜ ጸኒስ (በጸነሰች ጊዜ)፣ ድኅረ ጸኒስ (ከጸነሰች በኋላ)፣ ቅድመ ወሊድ (ከመውለዷ በፊት)፣ ጊዜ ወሊድ (በወለደች ጊዜ)፣ ድኅረ ወሊድ (ከወለደች በኋላ) ድንግል እመቤታችን ብቻ ነች ይልቁንም የኅሊና ድንግልናዋ እጅግ ያስደንቃል። የቤተክርስቲያን መጽሐፍ የእግዚአብሔርን የጥበቡን ምልዓት፣ ስፋትና ርቀት ሲናገር ከመጣ በኋላ የዓለምን ድንግልና ሲዘልፍ እንዲህ ይላል "ኅድግስ ዘከመገ ድንግልና እስመ ተደንገለ በሥጋሁ ወተማዕሰበ በነፍሱ" "እንዲህ አይነቱ ድንግልና ይቅር በሥጋው ድንግል ሆኖ በኃሳቡ ብዙ አግብቶ የፈታ ነው።" (ዜና ሥላሴ) ማለት ነው እመቤታችን ግን እንዲህ አይነት ሐሰብ አልነበራትም ከሴቶች ሁሉ ልዩ ናት ድንግልናዋም ከመውለዷ በፊት (ማቴ 1፥19) ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች (ሉቃ1፥26, ማቴ 1፥25) ከወለደችም በኋላ ድንግል ናት (ማቴ 1፥25) እስከ የሚለው ትርጉም ተደጋግሞ ስለተነገረ የሚያደናግር አይመስልም ካስፈለገም ማብራሪያ ጥቅሶቹ እነሆ (2ሳሙ 6፥20-23) ሜልኮል እስከምትሞት አልወለደችም ይላል ከሞተች በኋላ ወለደችን? (ዘፍ 8፥6) ቁራው ውኃው እስኪጉድል አልተመለሰም ይላል ከዚያስ ተመልሷልን? (ዘፍ፡18, መዝ 110፥1) ጠላቶችህን እግርህ ሥር እስክጥልልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ ይላል ከዚያስ ወልድ ቦታውን ይለቃል ማለት ነው? ከሚከተሉት ጥቅሶች

ጋር አነጻጽራቸው (ቈላ.2፥14, ዮሐ.7፥53) ሌላው በኩር የሚለው እንዳያደናግጠን በኩር ካለ ሁለተኛ ያስፈልጋል እንዳይባል በኩር ማለት ቀድሚያ የተወለደ ማለት ነው እንጂ የሚያስተረጉመው ማስከተልን ብቻ አይደለም የሚያሳየው (ዕብ.1፥6) ላይ ወልድን የአብ የበኩር ልጅ ይለዋል ሁለተኛ አለው ይሉ ይሆን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለድንግልናዋ በብዛት ተመዝግቧል። ከብዙ በጥቂቱ እየጠቀስን እንገልጻለን (ሕዝ.44፥1-4) "ወደ ምሥራቅ ወደሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ ቤተመቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር እግዚአብሔር ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል አለቃው ግን እርሱ በእግዚአብሔር ፊት እንጀራ ይበላ ዘንድ ይቀመጥበታል በበሩ ደጀሰላም መንገድ ይገባል በዚያም መንገድ ይወጣል" ይላል ነቢዩ ሕዝቅኤል።

ይህ መንፈሳዊ ቤት ሕዝቅኤል እንደተመለከተው እጅግ ድንቅ ቤት ነው። ቤቱም ዝግ ነበር የተዘጋውም እግዚአብሔር ስለገባበት ነው ነገር ግን ዙሪያውን የታጠሩ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ አጥሮች ነበሩ በአንድ በኩል ሦስት በአንድ በኩል ሦስት ደጀ ሠላሞች ነበሩ አለቃው ከአዳራሹ ውጪ በአጥሩ ውስጥ ገብቶ እንጀራ እንዲበላ ተፈቅዶለታል፤ ነገር ግን ከበላ በኋላ በዚያው በውጪ ይመለሳል ክርስቲያኖች ሆይ ይህ ምሥጢር ምን ይሆን እግዚአብሔር በተዘጋ መግባቱ የባህርዩን ርቀት ሰው አይገባበትም ማለቱ ሉዓላዊነቱን መልዕልተ ፍጡራን መሆኑን ያስተምራል ፍጻሜው ግን እንበለ ዘርእ ተጸንሶ እንበለ ዘርእ በኅቱም ድንግልና እንደሚወለድ ከተወለደም በኋላ እናቱ እንበለ ተፈትሆ-ማኅፀን እንደምትኖር ያስተምራል አምላክ ወሰብእ መባሉ ድንበር ልክ እንደሌለው ድንግል ወእም ለመባሏ ፍጻሜ የለውምና በምሥራቅ የተመሰለች ድንግል ናት። ድንግል ማርያም ምንም በአፍአ በጥበብ እግዚአብሔር እንድትታጭ ቢያደርጋት በውስጥ የብጽአት ልጅ ናት እና



እንደ እናቶቿ በዘር በሩካቤ መጽነስ በእደ ብእሲ መዳሰስ የለባትም የብፅዓት ልጅ ናትና መታጨቷ ገንዘቧ ሆኖ ሳለ አኗኗሯ ግን ከወለተ ዮፍታሔ በበለጠ በንጽሕና በቅድስና ነው። የብፅዓት ልጅ እንደሆነች እርሷ ራሷ "እፎኑ ይከውነኒ እንዘ ኢየምር ብእሴ" ማለት ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብላለች (ሉቃ.1፥34) ለብእሲ ታጭታ ከብእሲ ጋር እያለች ወንድ ስለማላውቅ ማለቷ እኔ የብፅዓት ልጅ ነኝ ተፈጥሮዬም መንፈሳዊ ነው ብቻን ጸንሶ መውለድ እንዴት ሊሆን ይቻለኛል ማለቷ አይደለምን? በሌላ በኩል ስንመለከት ደግሞ እመቤታችን የአብ ምሳሌ ናት የአብ ምሳሌ ስለሆነች ከሥጋው ቃል በቀር ለዕሩቅ ብእሲ እናት መሆን አትችልም ለአብ እንዳይቻለው። በንጉሥ ዙፋን ገበሬ በጳጳስ ዙፋን ቄስ ደፍሮ መቀመጥ እንደማይቻለው እንደዚሁም አምላክ በአደረበት ማኅጸን ተራ ሰው አያድርም ሰአሌ ሕጻናት በተሳለበት ሠሌዳ በተቀረጸበት ሰፋድል ዘርዐ ብእሲ ቀለም ሆኖ ሊሳልበት ሊቀረፅበት አይቃጣም አይታሰብም ዓውደ ማኅጸኗ አስቀድሞ በነቢያት ትንቢት ታጥሯል በብፅዓት ተቀጥሯል ተዘግቶ ይኑር አይከፈት ሰው አይግባበት የሚል አዋጅ ተነግሯል።

እንድትታጭ የተደረገበትም ምክንያት ስለሦስት ነገር ነው። መጀመሪያ መንፈሳዊ ጽንሱን ከሥጋውያንና ከአጋንንት ለመሠወር ሁለተኛ እርሷን ከውግረተ ዕብን ከጽእለት ለማዳን ሦስተኛ መከራዋ ብዙ ነውና እጬኛ አስመስሎ አጋዥ ረዳት ለመስጠት እና ፍጹም ሰው መሆኗን ለመግለጽ ነው፤(ትርጓሜ ሕዝቅኤል ይመልከቱ)

13. ምዕመናንና እመቤታችን፡- ሁላችን እመቤታችንን እንወዳታለን እናከብራታለን "ትምክህተ ኩልነ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ-አምላክን የወለድሽ እመቤታችን መመኪያችን ነሽ" እያልን እናወድሳታለን ምክንያቱ ግልጽ ነው አምላክን ጸንሳ ስለወለደች የሰው ልጆች የባህርይ ትምክህት የሆነውን ጌታ ስለተሸከመች ኀብስተ -

ሕይወት የሕይወት እንጀራ ከእርሷ ስለተገኘ ብርሃነ ሕይወት ከእርሷ ስለወጣ ሐረገወይን ከእርሷ ስለበቀለ ማየ ሕይወት ከእርሷ ስለመነጨ እግዚአ አጋእዝት የእርሷ ልጅ ስለሆነ ነው በሌላም በኩል ከእግረ መስቀሉ ስለተሰጠቻቸው ምዕመናን ይወዷታል።

በኢየሱስ ክርስቶስ የምናምን ሁላችን ድንግል እናታችን መሆኗን ልናምን ያሻል እነኋት እናትህ ብሎ ለዮሐንስ ሲሰጥ ዮሐንስን ለመሰልን እናት ሆናናለችና እነሆ ልጅሽ ብሎ ዮሐንስን ሲሰጣትም ልጆቿ ሆነናልና (ዮሐ 19፥29) ከዚያም በላይ በጸሎቷ እንማፀናለን "ሰአሊ ለነ ቅድስት" በማለትም ጸሎቷን እንሻለን "በእንተ ማርያም ጸዋሪትከ በእንተ ማርያም ሐጻኒትከ፣ በእንተ ማርያም ወላዲትከ" በማለት እንጸልያለን፣ ሕዋሳቶቿንም ማላጅ በማድረግ ስለተሸከመህ ስለማሕጸኗ፣ ስለጠባሃቸው ስለጡቶቿ፣ ስለአዩህ ስለ ዓይኖቿ በፊትህ ስለፈሰሰው ስለእንባዋ ይቅር በለን ይላሉ አሜን ስለእናቱ ይቅር ይበለን።

14. <u>ዕረፍተ ድንግል፡-</u> መተርጉማን አበው እንደሚተርኩት እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ድንግል ማርያም በተወለደች በስልሣ አራት ዓመቷ በዘመነ ሉቃስ ጥር 20 ቀን አርፋለች። አበው ስለዜና እረፍቷ የሚተርኩበት ትርጓሜ ውዳሴ ማርያም እንደገለጸው የድንግል ማርያም ዕድሜ 64 ሊሆን የቻለው ከወላጆቿ ጋር 3 ዓመት በቤተ መቅደስ፣ 12 ዓመት በቤተ ዮሴፍ፣ 9 ወር ከጌታ ኢየሱስ ጋር 33 ዓመት ከሦስት ወር ከጌታ ሞት በኋላ በቤተ ዮሐንስ 15 ዓመት ስለተቀመጠች ዕድሜዋ ተገናኝቶ 64 ዓመት ይሆናል። የእርሷን ስም የሚገልጹ የውዳሴ ጽሑፎችም በዕድሜዋ ልክ ተደርሰዋል ለምሳሌ የውዳሴ ማርያም ቍጥር 64 ነው የመልክዐ ማርያም ቁጥርም 64 ነው።



## <u>ጥቅስ በግዕዝ</u>

"ተገምረ ውስተ ማሕፀና ለእግዝእትነ ድንግል ንዕሕት ዘእንበለ ርኩስ ወላዲተ አምላክ ማርያም...ወይእቲአ ወላዲተ አምላክ ይእቲ ዘበአማን ወእምኀድረ ወሊዶታሂ ድንግል ይዕቲ ወኢተወለጠ ማኅተመ ድንግልናሃ ወአልባቲ ርስሐት ለግሙራ ዘእንበለ ደነስ። ሐንጸ ሎቱ ለርእሱ ሥጋሁ ቅዱሰ እምሥጋሃ ወደመ ለድንግል። ኦ ማኅፀን ቅዱስ ዘተጽሕፈ ውስቴቱ መጽሐፈ ግዕዛን እንተ ዘኲሎ እጓለ እመሕያው። ኦ ማኅፀን ቡሩክ ዘኀደረ ውስቴቱ ንዋየ ሐቅል ዘይትቃወሞ ለሞት ዘተሠልጠ ላዕሌነ ኦ ገራህት ኅሪት ዘአፍረየት ለነ ዘርዐ እምነ ዘራዒ በህላዌሁ ዘእንበለ ዘርዕ ከመ ሰዊት ኦ መቅደስ ዘኮነ ሎቱ እግዚአብሔር ካህነ ዐቢየ እንዘ ኢይትዌለጥ ኀላዌሁ አላ ባሕቱ በእንተ ምህረቱ ወተሣህሎቱ ለብሰ ሥጋ ለተክህኖ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ..."

<u>ትርጉም፡-</u>

ያለዘርአ ብእሲ አምላክን በወለደች፣ መለወጥ በሌለባት በድንግል ማርያም ማሕፀን ተወሰነ...እሷም በእውነት ወላዲተ አምላክ ናት ከወለደችውም በኋላ ድንግል ናት ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም፣ ፈጽሞ ነውርም የለባትም...ከነፍሷ ነፍስ ከሥጋዋ ሥጋ ነሥቶ ሰው መሆኑን ሊክስበት ፈጥሮ ተዋሐደው... የሰው ሁሉ ነፃነት የተጻፈበት ቅዱስ ማሕፀን እንደምን ያለ ነው? በእኛ ሠልጥኖ የነበረ ሞትን የሚቃወመው የጦር እቃችን (ክርስቶስ) ያደረበት ቡሩክ ማሕፀን እንደምን ያለ ነው?

እንደ ዕፀ ሠሉስ ያለዘርዕ በባሕርዩ ሁሉን በሚያስገኝ በመንፈስ ቅዱስ ጌታን ያስገኘችልን የተመረጠች ገራሕተ ሠሉስ (እርሻ) ድንግል ማርያም እንደምን ያለች ናት? እግዚአብሔር እንደ ቸርነቱና እንደ ይቅርታው እንደ መልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት ለማገልገል ሥጋን ለብሶ፣

ባሕርዩ ሳይለወጥ ታላቅ ካህን የሆነበት መቅደስ እንደምን ያለ ነው? (ሃ. አበው ዘአክርስቶዶሎስ ም.112 ቁ.18-24)

ጸጋ ዘአብ ሂሩት ዘወልድ ሱታፌ ዘመንፈስ ቅዱስ ወበረከታ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል በክልኤ ተፋቅሮ ዘነቢያት ወዘሐዋርያት ዘጻድቃን ወዘሰማዕታት ወዘአበው ቀደምት ወትረ የሃሉ ምስሌነ አሜን።

*የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነት የመንፈስ ቅዱስ አንድነት በሁለት ወገን ድንግል የምትሆን የእመቤታችን የድንግል ማርያም በረከቷ የነቢያት የሐዋርያት የጻድቃንና የሰማዕታት የቀደሙ አባቶችም ፍቅር ዘወትር ከሁላችን ጋር ይሁን።*

አሜን!

**ጥያቄዎች**

1. ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?
2. ድንግል ማርያም መች ተጸነሰች?
3. ወላጆቿ ማን ማን ይባላሉ?
4. እድገቷ እንዴት ነበረ?
5. የገብርኤል የሰላምታ ቃላትስንት ናቸው?
6. የአካላዊ ቃል ጽንሰት እንዴት ነበር?
7. የመንፈስ ቅዱስ ግብር ድርሻ ምንድን ነው?
8. ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን በተመለከተ ምን አነበቡ?
9. የቤተክርስቲያን እና የእመቤታችን እናትና ልጅነትን በተመለከተ ምን አነበቡ?
10. ድንግል መቼ አረፈች እድሜዋስ ስንት ነበር?


መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
U.S.A.